# ዛሬ ኢትዮጵያ በምትገኝበት ተፈታታኝና ወጣሪ ሁኔታ ኢ.ሕ.አ.ፓን መተንኮስ ለምን አስፈለገ?

## (ፍየል ወዲህ፣ ቅዝምዝም ወዲያ!)

ታምሩ ባልቻ

ኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆቹ እየተፈጁበትም አዳዲስ ትውልድ መተካቱን አያቆምም። ዛሬ በሀገራችን ዉስጥ እያደገ፣ እያወቀና እየጎመራም በመምጣት ላይ ያለው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ስለ ቀዳሚው ትውልድ፣ መጥፎውንም ሆነ ጥሩውን ታሪኩን ማወቁ የማይቀር ነው።

ኢ.ሕ.አ.ፓን ጭምር ስላካተተው ትውልድ፣ በተለይም የትውልዱ ፈርጦች ከነበሩት፣ ከኢ.ሕ.አ.ፓ አባላት የሀገራዊ ለውጥና ዕድገት ራዕይ፣ እምነትና ገድሎች ትክክለኛውን ነገር አዲሱ ትውልድ ማወቅ ይገባዋል::
ኢትዮጵያችን እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ላባዕዳን ተገዥም ተንበርካኪም አልነበሩም። የአድዋ ድል ባለቤቶችንና ወራሾቻቸውን ያፈራች ሀገር ነች። እነራስ አሉላ አባ ነጋን፣ አፄ ቴዎድሮስንም ያፈራች ሀገር ነች። በርካታዎቹ የኢህ አፓ አባላትም የነዚያን ጀግኖቻችንን በጎ ዓርአያ የተከተሉ አናብስት ነበሩና ኢትዮጵያን የሚጠሉ ሁሉ ክፉኛ ነው እነሱንም የጠሏቸው!? ዛሬ ባዕዳን ሃይሎች ሌላ በራሱና በማንነቱ የሚኮራ፣ እነሱንም “ዞር በሉ የሀገሬ ባለቤት እኔው ነኝ” የሚላቸው ሃይል፣ እንዲበቅል ይሻሉ ማለት ዘበት ነው።

የሚዳፈራቸው የጥቁር ሀገር መሪና ትውልድም መቼም በየትም፣ ግድ ካልሆነባቸው በስተቀር፣ ማየት አይፈልጉምና!! የጥቁር ሕዝብ፣ የአፍሪካ፣ የኢትዮጵያችንም ታሪክ በደም ጎርፍ የረሰረሰ ነው። አዲሱ ትውልድ ከኢሕአፓ ስህተቶችም ሆነ አኩሪ ገድሎች፣ ራሱ መርምሮና አበጥሮ እንዳያውቅ፣ በተለይም በጎውን ጎኑን እንዳይወስድ ሙሉ ታሪኩን ጠለሸት በማልበስ ለማዳፈን የሚሞከረው። ማናቸውም ባዕዳኑ፣ ወይም ሀገር–ጠል የሀገሪቱ ተወላጆች፣በአጋፋሪዎች መሣሪያነት በኢሕ አፓ ጀግኖች ገድል ላይ የረጩትን በካይ አሉባልታ ማምከን፣ ያወረዱትን ጭጋግ መግፈፍ ያስፈልጋልና በመጀመሪያ ስለ ኢሕ አፓ (የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ) አባላትና “ስለዚያ ትውልድ” ከፊሉ፣ ለየት ያለ ታሪክ ስላላቸው ስለጠባቦቹ ሳይሆን፣ ስለአብዮታውያኑና ሀገር–ወዳዶቹ፣ በመጠኑ የምንለው አለን።

በታተሙ አያሌ መጻሕፍት፣ በምንባቦችና በቃል ትረካዎችም “ያ ትውልድ” በመባል የሚታወቀው፣ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1960ዎቹ እስከ 1980ዎቹ ዓ.ም. ድረስ በነበረው ወቅት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ አዲስ–አበባ ዩኒቨርስቲና በሁሉም የሀገሪቱ ኮሌጆች ዉስጥ እንዲሁም በውጭ ሀገሮች ለከፍተኛ ትምህርት ተልከው ከነበሩት አብዛኛዎችን፣ በወጣትነት የዕድሜ ክልል የነበሩትን ምሁራንና የመንግሥት ሠራተኞችን፣ በአገልግሎትና በየፋብሪካዎችም ሠራተኞች ከነበሩት ሰፋ ያለውን ክፍል ያካተተ ስለሆነም በወቅቱ ከነበረው ወጣት ትውልድ በርከት ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍል የያዘ ነበር። በየትምህርት ተቋማት ዉስጥ እየተማሩ የነበሩትን በስፋት ያሳተፈ፣ በሥራ ላይ ተሰማርተው ከነበሩት ደግሞ ለመሠረታዊ

ለውጥ የቆሙትን የማይናቅ ቁጥር የያዘና በትግሉ ያሳተፈ፣ ሠፊ የኅብረተሰቡ ክፍል ስለነበር በዉስጡም ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ያነገቡ ክፍሎች ነበሩ።

ከዚህ ለለውጥ የተነሳሳ ሠፊ ትውልድ ዉስጥ ነው፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰባዊና ባህላዊ ለውጥ ለማምጣት ከሚፈልገው ክፍል የፖለቲካ ንቃታቸው ላቅ ያለው ቀዳሚነቱን የያዙት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ዉስጥ ተደራጅተው መንቀሳቀስ የጀመሩት። ከእነዚህ መሐል ጎልተው የወጡት ሁለት ማርክሳዊ የነበሩ ድርጅቶች፣ ኢሕ አፓና መ ኢሶን ነበሩ። አሁን በዚህ አጭር መጣጥፍ የምንናገረው የኢትዮጵያ ግልጽና ስውር ጠላቶች በጣም ስላተኮሩበት፣ ከሁለቱ አንዱ ስለሆነው፣ ስለኢሕ አፓ ነው። በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተፈጠሩ፣ በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ወይንም በጾታ ልዩነቶቻቸው ላይ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው፣ በሀገር–አፍቃሪነታቸው፣ በለውጥ ፈላጊነታቸው፣ ለእኩልነት፣ ለማኅበራዊ ፍትኅና ለሁለንታዊ ለውጥና ዕድገት ባላቸው ራዕይ ላይ በመመሥረት፣ ነበር አብዛኛዎቹ ተፈላልገው በመገናኘት፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ.) ዉስጥ የተደራጁት።
በርካታዎቹ በቅድመ–ፓርቲ ምሥረታ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴና በትምህርት ተቋማቱ ዉስጥ የመተዋወቅ እድልም ነበራቸው። በወቅቱ በሀገራችን ዉስጥ የነበረውን የጉልተኛ ሥርዐት ለመለወጥና፣ በተለይም ለሠርቶ–አደሮችና ለሠፊው ጭቁን ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚበጅ ሥርዓት ለመፍጠር፣ … አስበው፣ ዐልመው፣ ቆርጠው ተነስተው አምርረው ታግለዋል፣ እጅግ ከባድ መሥዋዕት ከፍለዋል።
የእነሱን ትግልና ሁኔታዎች መገምገም የሚገባው ታዲያ ያኔ በነበረው የኢትዮጵያ፣ የአካባቢያችንና የአፍሪካ፣ ከዚያም ሰፋ ያለውን የዚያን ጊዜውን የዓለም ሁኔታ ጭምር በማገናዘብ ሊሆን ይገባል። የእነዚያን አብዮታውያን ተግባሮች ለመተቸት ደግሞ ቢያንስ ተቾው ኢትዮጵያዊ ሰብእና ያለው፣ ራሱ በዚያን ወቅት ቀይ ደምም ሆነ ቀይ እምባ ያላስፈሰሰ፣ ቀናና ሚዛናዊም አስተሳሰብ፣ ማለትም የሞራል ብቃት ሊኖረው ይገባል እንላለን። እንደ ዕውነቱ ከሆነ በወቅቱ ኢሕ አፓ የታገለው ኢትዮጵያ ዉስጥ የነበሩትን ጉልተኞችንና ሥርዓታቸን ብቻም አልነበረም። እነሱን ያግዙ የነበሩትን የውጭ ሃይሎችንም ጭምር ነበር። አንዳንዶቹ ወገኖቻችን፣ ተታለውና መስሏቸው፣ ወይንም ዐምነው አለዚያም በጥቅም ተገዝተው፣ ይታዘዟቸውና ያገለግሏቸው የነበሩትን፣ አሜሪካንና ሌሎችንም የምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶችም ኢትዮጵያ ላይ የነበራቸውን ጫና ጭምር በመቃወም ነበር ያያኔው ቁርጠኛ ኢትዮጵያዊና ሀገር–ወዳድ ትውልድ፣ የኢሕ አፓም አባላት ጭምር የታግሏቸው። ኢሕአፓ በዚያን ጊዜ “የሶቭየት ኅብረት” ይባል የነበረውንም “ሶሺያል ኢምፔሪአሊስት” አዝማሚያዎች ስለነበሩት፣ በእሱ ይመራ የነበረውን ጎራም፣ በምዕራባውያኑ ምትክ ኢትዮጵያ ላይ ጫናውን እንዳይፈጥር ይፈልግ ስለነበር ራሱን ከእነሱም “ወዳጅነት” እየተከላከለ ነበር የሚጓዘው።
በቻይናና መሰሎቿ ጭፍን ቀኖናዊ አስተሳሰብ ስር ሳይወድቅ፣ ሆኖም ግን ግንኙነቶችን ከአብዛኛዎቹ ሶሺያሊስት ሃይሎች ጋር ፈጥሮ ነበር ኢ ሕ አፓ ይጓዝ የነበረው። በኢትዮጵያውያን የራስን ነፃነትና ክብርን የመጠበቅ እሴት ትልቅ ዕምነት፣ የነበረውና ዛሬም ያለውም ድርጅት ነው። ራሱ ትክክል ነው ብሎ በሚያምንበት አስተሳሰብና አተረጓጎም፣ በማርክሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮት፣ እየተመራ ለማንም ሳያጎበድድ፣ የማንም ታዛዥና ሎሌ ሳይሆን ነበር ኢሕ አፓ ይታገል የነበረው። ከሁሉም የውጭ መንግሥታት ጋር፣ ከዋናዎቹ ኢምፔሪያሊስቶቹ መንግሥታት በስተቀር፣ በየሀገሩ ከነበሩ በርእዮተዐለም ከሚቀራረባቸው የፖለቲካ ሃይሎች ጋር ግንኙነቶች ነበሩት።

ሠፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ስለነበረው፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ ኤምባሲዎች ያሏቸው መንግሥታት ደግሞ፣ ይህንንም ያውቁ ነበርና ኢሕአፓ የመንግሥት ሥልጣን ሊጨብጥ ይችላል ከሚል ግምታቸው አኳያ የውጭ መንግሥታትን ለመገናኘትም ችግር አልነበረውም።

ከውጭ መንግሥታት ጋር ሲገናኝ ደግሞ አምባገነኑን ደርግ ማስፈቀድ አያስፈልገውም ነበር! ኢ.ሕ.አ.ፓ. ያለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ የነበረው፣ በመላ ሀገሪትዋም ቅርንጫፎች የነበሩት፣ ኅብረብሔር ፓርቲ ስለነበረ፣ በዚያን ጊዜ ስለነበረችውና ስለወደፊትዋ ኢትዮጵያ የሚያስብና የሚጨነቅም ፓርቲ ነበር። በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ላይ ከማንም ባዕድ ጋር፣ ወይንም ኢትዮጵያ ዉስጥ ከተቋቋመ የብሔር/ብሔረሰብ ነፃ-አውጭ ነኝ ከሚል ድርጅት ጋር፣ ያልተደራደረና ያልተጎናበሰም፣ ለመላው ሕዝብ የጋራ መብት፣ ለእኩልነቱም ጭምር እንዲሁም ለሀገሪቱ አንድነት ሉዓላዊነት ክብርና ጥቅም የቆመና የተፋለመም ፓርቲ ነው።

ስለኢሕአፓ ትክክለኛ አቋሞችና በወቅቱ በርካታ መስዋዕት የከፈለባቸው አኩሪ ተግባሮች ለአዲሱ ትውልድ ይረዳ ዘንድ አንዳንድ ሃቆችን ከዚህ በታች በማሳያነት እንጠቅሳለን። አንጎላቸውን በወታደራዊ ጡንጫቸው የቀየሩት የደርግ አባላትም (መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች)፣ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያንን ሁሉ ጥፋት አድርሰው እስከዛሬ ይዋሻሉ፣ ዛሬም ወጣት አብዮታውያኑን አድነው እየጨፈጨፉ "የፍየል ወጠጤ ….. " የሚል ሞት-አርጂ መዝሙራቸውን እያዘመሩ የሚፎክሩም፣ የሚያቅራሩም ይመስላሉ።

የተወሰኑት ደግሞ፣ ለውጥና ዕድገት ታሪካዊ ክስተቶች መሆናቸውን፣ አዲስ ትውልድ አዳዲስም የተለመዱም ጥያቄዎችን ሊያነሳም እንደሚችል ካለማወቅ፣ ያ ትውልድ፣ በተለይም እንደ ኢሕ አፓ ዐይነት የፖለቲካ ድርጅቶች "ለለውጥ ባይነሳሱ ኖሮ …" ብለው የሚያስቡ፣ ከኋላቀርነት በመንደርደር ለውጥ በአንዱ ወይንም በሌላው መልክ እንደሚመጣ ካለመረዳት፣ ከዕዕምሮ እንጭጭነት፣ ሊሆን ይችላል። ከፊሉ ደግሞ ከርእዮተ ዓላማዊ ባላንጣነት፣ወይንም ከተንበርካኪነትና የባዕዳን "ኒዎ-ሊብራል" አስተሳሰብን "ያመነ ይድናል" ብለው፣ ሃሳቡ አዲስና ዕውነት መስሏቸው፣ ፈቅደው የኢምፔሪአሊስቶቹ አገልጋይ የሆኑ ወገኖችም አሉ። ሁሉም ደግሞ እንደ ውዳሴ የሚያዜሙት፣ "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት፣ እስከመገንጠል" የሚለውን ሀረግ ያመጣው፣ ያቀነቀነው፣ ያስለመደው፣ ወ.ዘ.ተረፍ ኢ ሕ አ ፓ ነው እያሉ ነው። ይህ ቀመራቸው ግን ሙሉ በሙሉ ሃሰት ነው።

ዓላዋቂዎች ወይንም ዋሾዎች ናቸው ማለት ነው። ሀረጉ ኢሕአፓ ከመመስረቱ (1964 ዓ.ም.) በፊት ሀገራችን ዉስጥ ገብቶ ነበር። ኤርትራን ለመገንጠል የተነሱት "የነፃነት-ግንባሮች" ኢሕ አፓ ከመመሥረቱ በፊት ነበር ተደራጅተው የትጥቅ ትግል የጀመሩት። ኦጋዴን ውስጥ በከተል ጣሂር ይመራ የነበረው እንቅስቃሴም ከኢሕአፓ ምሥረታ በፊት ነበር የተነሳው።ግልጥ ባለ በብሔረሰብ ነጻ-አውጭ ስም ባይሆንም ጸረ ብሄር ጭቆና እንቅስቃሴ በኦሮሞ ኢትዮጵያውያን "በሜጫና ቱለማ የባህልና የልማት ማኅበር" ስያሜ ይደረግ የነበረው ኢሕ አፓ ከመመሥረቱ በፊት ጀምሮ ነበር። በኋላም በዋቆ ጎቶ ይመራ የነበረው የባሌ እንቅስቃሴ ከኢሕአፓ ምሥረታ በፊት የነበረ ነው። በርግጥም ኢሕ አፓ በተደራጀበት ጊዜ በማርክሲስት-ሌኒኒስት አስተሳሰብ ይመራ ስለነበር፣ በዚያን ጊዜዋ ኢትዮጵያም ዉስጥ የብሔር ጭቆና አለ ብሎም ያምን ስለነበር፣ በርግጥም "የብሄር ብሄረሰብን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፣ እስከ መገንጠል" ያለ መብት፣ በመርኅ ደረጃ ኢሕአፓ ተቀብሎት ነበር።

አንደኛ ለብሔር ጭቆናው ሃላፊነቱን ያስቀመጠው "የመሳፍንት ወይም ፊዩዳል ገዥ መደቡ" ላይ ነበር፤ አንድ ብሔር ላይ ብቻ አይደለም። ሁለተኛ ሃሳቡን ያቀነቀነው በመርህ ደረጃ እንጂ በተግባር ከኢትዮጵያ የመገንጠልን ጥያቄ ለማንም ድርጅት ወይም

ሃይል ወይም መንግሥት፣ ምንም ጊዜ አልደገፈም፣ አልተቀበለም። ኢሕ አፓ ምንም እንኳን የብሔር ጭቆናን ማወቅና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ማወቅ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን እንደሚያቀራርብና በመሀከላቸውም መተማመንን እንደሚፈጥር ቢያውቅም፣ መብቱን ካወቀ በኋላ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። በዚያው መጠን ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ተጠናክረው በመታገል በሀገሪቱ ዉስጥ መላው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቱንና እኩልነቱን እንዲቀዳጅ ለማድረግ ከታገሉና፣ ሕዝቡም መብቱን ከተቀዳጀ የመገንጠሉ ጥያቄ አቀንቃኞችን የሚደግፍበት ምክንያት አይኖረውም። ሕዝቡ ጭቆናው አለ ብሎ ስለሚያምን፣ የለም አልተጨቆንክም ማለቱ ትክክልም ተገቢም አልነበረም።

ለነገሩ እስከዛሬም ምንም ጭቆና አልነበረም የሚሉም አሉ። በርካታው ሕዝብ ጭቆና መኖሩን ዕውነትም ስለሆነ አምነህ አብረን በጋራ ትግል እናጥፋው ስትለው ድጋፉን ይሰጥሃል፣ ወደ ተገንጣዮች ሊሄድ የሚችለው ድጋፍም እየቀነሰ ይመጣና ጥያቄውም፣ የዴሞክራሲያው መብት መረጋገጥ፣ የእኩልነት፣ የፍትኅ ይሆናል። የተገንጣዮች አስተሳሰብና ጎራም እየተዳከመ በመምጣት እንደሚመክንም ኢ.ሕ.አ.ፓ. አጥብቆ ያምን ነበር። በረጅም ታሪኩ ዉስጥ እርስ-በርሱ እየተዋሀደና እየተጋመደ የመጣውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባብሮ፣ አደራጅቶ በማታገል የሀገሩ፣ የእኩልነቱና የሌሎችም መብቶቹ፣ የነፃነቱ፣ የክብሩ፣ የጥቅሞቹም ሙሉ ባለቤት ማድረግ ነበር ዋናው የ ኢሕአፓ ዓላማ። የመገንጠል ሃሳብ ያቀነቅኑ የነበሩት ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ድርጅቶች እንዲሁም እነሱን ይደግፉና ይረዱም የነበሩ የውጭ መንግሥታት ከደርግ የበለጠ የፈሩትና የታገሉትም፣ የሁሉንም ብሄረሰቦች ድጋፍ እያገኘ የመጣውን፣ ኢሕአፓን ነበር።
የየብሔረሰቡን አካባቢ "እየከለሉ"፣ ሕዝቡንም በየብሄሩ ነጣጥለው ሊይዙት የሚፈልጉት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያቆጠቆጡ ራሳቸውን "የየብሔረሰቡ ነፃ-አውጭ" ያደረጉ ቡድኖች፣ ሁሉም ማለት በሚያስችል ደረጃ፣ ኢሕአፓን እንደ ተቀናቃኝ ብቻ ሳይሆን እንደ ጠላት ነበር ያዩት። እነሱ ኢትዮጵያዊነቱን አስጥለው ሌላ ሊያደርጉት የሚፈልጉት ሕዝብ፣ በሁሉም ብሄረሰቦች ዙሪያ ግን ኢሕአፓ ጥሩ ወዳጅነትና ፍቅር ተችሮት ስለነበር፣ ጠባብ ብሔረተኞቹና ተገንጣዮች ሊገነቡት ያሰቡትን ግድግዳ እየናደባቸው ስለነበር ነው። ሕዝቡን በመቅረብ፣ በማሳመን፣ ከውስጡም አባላቱን በመመልመል፣ በማደራጀት፣ የወደፊትዋን በሕዝቡ እኩልነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያ በኅብረ-ብሄራዊ ድርጅቶችና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አውድ አማካይነት መፍጠር ስለጀመረ ነበር የጠባብ ብሔረተኞች ጠላት ተደርጎ የታየው።

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ፣ ያኔ እንደ አሁኑ በሀ.ወ.ሓትና በሻዓቢያ ሆን ተብሎ በተፈጠረ ጸረ-ኢትዮጵያ አረንቋና ዝብርቅርቅ ያለ ሁኔታ ሳይፈጠር፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኅብረ-ብሄራዊ ኅላዌ፣ የሕዝቡ አንድነት፣ የሀገር አንድነት ጉልህ ዕውነታዎች እንጂ አዲስም አስቸጋሪ ነገሮች አልነበሩም፣ የአብሮነት ታሪካችን ጥሩ ምርቶችም ስለሆኑ!! ደርግ የተባለ ወታደራዊ ቡድን፣ በኢትዮጵያ አብዮታውያን ከተነሱት መፈክሮች ጥቂቱን ቀምቶ መጠቀሚያው ለማድረግ እየሞከረ፣ አብዮታውያኑን ራሳቸውን ግን ያለ አንዳች ርኅራኄ እየጨፈጨፈ፣ ኢትዮጵያን ለዛሬው ሁኔታ አበቃት። ከአብዮታውያኑ ዋና ዋና ጥያቄዎች፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን መከበር ጭምር፣ ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ ሀገራችን ዛሬ ለምናየው የአጥፊዎች መለማመጃም አትሆንም ነበር።

ሀገራችን ዉስጥ የተካሄደውን ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ደርግ በእመቃ፣ ግድያና ጭፍጨፋ ነው ያሰናከለው። ከህዝቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች መሀል አንገብጋቢ የነበረውን መሬትን ለአራሾች አከፋፍሎ ሲያበቃ፣ ሕዝቡ የጠየቀውን የዴሞክራሲ፣ የእኩልነት፣ የፍትኅ፣ ጥያቄዎች ግን ባለመመለስ፣ የሥልጣን አባዜ ይዞት፣ አተብቶትና አቅበዝብዞት፣ አምባገነናዊ ሥርዓቱን

በመላው ሕዝብ ላይ ጫነ። አፈና፣ ድብደባ፣ እስራት፣ ሰቆቃ፣ ጅምላ-ጭፍጨፋ ሙብት በጠየቁ ወጣት አብዮታውያኑ ላይ ለዐመታት “ቀይ ሽብር” ብሎ የሰየመውን መተራ በማካሄድ፣ ሀገሪቱን ለውድመት፣ ለትዝብትና ለውግዘትም አበቃት።

የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮትም በጸረ-አብዮታዊ ዘግናኝ ግብሮች አስጨነገፈው!! እነዚህ ነፍሰ-ገዳዮችና ሰው-በላዎች፣ አንድ ትውልድ፣ ያውም የወገንና የሀገር ፍቅር ያንደገደገው አብዮታዊ ትውልድ፣ መተሩ። አንዳንድ የቀድሞ የደርግ ባለሥልጣኖች፣ ያኔ የሠሩት ግፍ እያባነናቸው ይመስላል ወደር-በሌላቸው የኢትዮጵያ ብርቅ ልጆች ላይ፣ በአርበኞችና ጀግኖች ላይ ይኸው ዛሬም፣ ያኔ ትውልዱን በሙሉ ገድለው ስላልጨረሱ ተቆጭተው የሚቀባጥሩ በሚያስመስል ደረጃ፣ እየታገሉ ባሉት፣ የኢሕ አፓ አባላት ላይ፣ የሀሰት ክሶችን ይደረድራሉ። ያውም ከደርግ የከፋ፣ ኢትዮጵያውያኑን ርስብርስ አጋጭቶ፣ አንደኛውን ብሄረሰብ በሌላው ላይ አነሳስቶና አስታጥቆም፣ አንዳንዴም ራሱ አንዱን መስሎ ሌላውን በመውጋት፣ እያጫረሰ ያለና፣ ያለምንም ርህራሄ የሚቃወሙትን ሁሉ በሚያዛቸው የፀጥታና የታጠቀ ሃይሎች ሊጨፈጭፍ በዝግጅት ላይ ያለ፣ የሀገሪቱን አንድነትና ኀላዌም የቻለውን ያህል እያጠፋ ያለ አምባገነናዊ እኩይ የዘውግ ቡድን፣ የኢትዮጵያችን ገዥም አጥፊም ሆኖ በሚገኝበት ወቅትና ሁኔታ፣.. የደርግ ነፍሰ-ገዳዮች ርስ-በርሳቸው ከሚቀባበሉት የሃሰት ክስ ውጭ አንድም ማስረጃ ሳያቀርቡ፣ ማስረጃ የለምና ከየትም ሊያመጡ አይችሉም፣ በስም ማጥፋት ዘመቻቸው ደጋግመው ይተነኩሱናል። በተለይ መልካም ተግባርና ጥሩ ገጽታዎች እየራቁት እመጣው፣ አሜሪካ ጉያ የተወሸቁት አንዳንድ አወዛጋቢ ሰብዕና ያላቸው ግለሰቦች መዘባረቃቸውን አቁመው አርፈው መቀመጡ ይሻላቸው ነበር። በሀገር-ወዳድነት ሌላውን ሊከሱ ይዳዳቸዋል። “የአባዬን እከክ በማዬ ልከክ” ይሏል ይህ ነው።

ልትደብቁት የማትችሉትን ነውራችሁን ማዝረክረክ ከባድ አይሆንም። አሁን በጣር ላይ ያለውን፣ ህ.ወ.ሓ.ትን ለማገዝ፣ በነዚያ “ኢትዮጵያን ቢያጠፋ ምን ቸገረን፣ ለእኛ የጸረ-ሽብር ትግል መሣሪያችን ሆኖ እስከተላላከንና እስካገለን ድረስ ድረስ” የሚሉትን ዛሬም በድጋሚ የነሱኑ ተልዕኮ ተቀብላችሁ ይሆን?! የአሁኑ ወቅት ያለጥርጥር፣ ሁሉም ሀገር ወዳድ ተባብሮና ተከባብሮም ዋናውን የጥፋት ሃይል ለመታገል ቅድሚያውን መስጫው ወቅት ነው። በተለይም ደግሞ ሤረኛ፣ ጎሠኛና በርግጥም ፀረ-ሠላም፣ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ህዝብዋም የሆነውን የህወሓትን ገዳይ ቡድን በመታገል ላይ መረባረብን ነውና ወቅቱ የሚጠይቀው። ታዲያ በጥባጭ ካሉ ጥሩ ወህ አይጠጣም እንደሚባለው፣ አንዳንድ ወቅትና ሁኔታን ማገናዘብ የተሳናቸው፣ ወይንም ሌላ ዓላማ ያላቸው ተንኳሾችና ነውረኛ ግለሰቦች በትግል ሜዳ በወደቁ ጀግኖችና ሀገር-ወዳድ የኢሕአፓ አባላት ላይ የውሸት ክምር በዚቹ በአሁንዋ ወቅት ስለቆለሉ፣ ዕውነቱን፣ የነበረውን ሁኔታ፣ የጀግኖችን ገድል በከፊልም ቢሆን፣ ይፋ አውጥቶ በመናገር ይህንን የተነዛውን ሃሰት ባዶነት ማሳየት የኛ በሕይወት ያለነው ጓዶቻቸው የሞራልና የፖለቲካም ሃላፊነት ስለሆነ፤ የነዙትን የውሸት ትቢያ ዕውነተኛውን የኢሕአፓን የያኔ ጊዜውን አኩሪ ታሪክ፣ በመጠኑም ቢሆን በማሳወቅ፣ የከንቱዎችን የማጠልሸት ግባቸውን ማምከን ግድ ሆኖብን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ሲፈጠርለት ሁሉንም በየስራው እየመረመረ ሊዳኘው ይችላል፤ ወቅቱም እየቀረበ እንጂ እየራቀ በመምጣት ላይ አይደለም።

አሁን ሁላችንም ወገናችንን እንወዳለን፣ የተወለድንባትንም ሀገር ባንወዳት እንኳን አንጠላትም ካልን፣ እስቲ ርስ-በርስ መቋሰሉን ለጊዜው ተወት አድርገን፣ ሀገርንና ሕዝብን እያጠፋ ያለውን፣ ህ.ወ.ሓ.ትን፣ የወቅቱን ዋና ጠላት እንደየችሎታችን እንታገል። የደርግ ባለሥልጣናት የነበራችሁና ኢ.ሕ.አ.ፓን፣ አላጠፋችሁትም፣ ምን ጊዜም አታጠፉትም፣ ታዲያ ይብቃችሁ፣ ተወት አድርጉን። “ጥፋት እስከ መቃብር” ቢያስነውር እንጂ አያኮራም። አንድ ጀግና ትውልድ፣ ያውም ሀገሩንና ወገኑን አጥብቆ የሚወድ፣ ትውልድ መትራችሁ ሀገሪቱን ባዶዋን አስቀራችኋት። ጀግኖችን በመግደል፣ ሀገሪቱን የሀገር-ወዳዶችና

የጀግኖች ደሀ አደረጋችኋት። የዛሬዎችን፣ ሀገር አጥፊዎች፣ የተፈጠሩባትን ውድ ሀገራችንን ለማጥፋት ሳይታክቱ እየተውተረተሩ ያሉትን፣ የህ.ወ.ሓት ባንዳዎችንና፣ አጃቢዎቻቸውን፣ አምርሮ እየታገለ፣ ከፍተኛ መስዋዕት እየከፈለም እየተዋደቀ ያለውን የዛሬ ወጣት ትውልድ፣ ስለ ኢሕአፓ እናንተ የምትዋሹትን ሳይሆን ትክክለኛውን ታሪክ፣ ሃቁን እንዲረዳ ከመፈለግ ብቻ በመነሳት፣ (ሆን ብለው የሚዋሹትን ለማሳመን ሳይሆን)፣ ከኢሕአፓ ዕምነቶችና አቋሞች፣ ፈተናዎችና ገድሎች አንዳንድ ምሣሌዎችን እናንሳ። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ከኤርትራ ግንባሮች፣ ከሁለቱም ዋና ዋናዎቹ ጋር፣ ግንኙነትና ዉሱን ትብብሮች ቢያደርግም፣ ምንም ጊዜ ከማንኛቸውም ጋር፣ ሀ) "ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች" የሚለውን ጥያቄያቸውን ኢሕአፓ እንደ ድርጅት ተቀብሎት አያውቅም፣ ለ) የኤርትራን የመገንጠል ጥያቄ ተግባራዊነት (ከንድፈሃሳብ ውጭ) አልደገፈም፣ ሐ) በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ 1982 ዓ.ም. ጀምሮ የኤርትራ ጥያቄ በኢትዮጵያ ዉስጥ በፌዴራላዊ ሥርዓት ምሥረታና በአንዲት ኢትዮጵያ ማዕቀፍ ሊፈታ ይችላል የሚል ይፋዊ አቋም ሲያራምድ ቆይቷል፣ መ) ኤርትራ በሀገር በቀል አስገንጣዮች፣ በባዕዳን አጋፋሪነት፣ ባዕዳኑን በሚታዘዙ መሣሪያነት፣ ነፃነትዋን ካወጀችም በኋላ ኢሕአፓ እስከዛሬ ያንን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በሌለበት የተደረገ "ሬፈረንደም"ና ውጤቱን ዕውቅና አልሰጠም።

ሁለቱም የኤርትራ ግንባሮች በተለያዩ ወቅቶች ካደረጉለት ትብብሮች የገዘፉ አያሌ መሠናክሎችንም በተለያዩ ወቅቶች ደቅነውበታል፣ ጉዳቶችንም አድርሰውበታል። ደርግ እየተሸነፈም እያለ ኢህአፓን ከመዋጋት ተቆጥቦ አያውቅም ነበር። በ 1983-84 ዓ.ም. በህ.ወ.ሓ.ት.፣ በሱዳን መንግሥትና በህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዓቢያ) የተጣመረ ሃይል ነው ኢሕአፓ/ኢሕ አሠ ጎጃምና ደቡብ-ምዕራብ ጎንደር ዉስጥ በተደረጉ በርካታ፣ ከባድ ጦርነቶች ተዋግቶና ከባድ መስዋዕት ከፍሎ ነው በመጨረሻ በጥምረቱ ሃይል የተሸነፈው?! ደርግ ፈራርሶ፣ መሪዎቹ ሀገር ጥለው ከሸሹም በኋላ ኢሕአፓ ከህ.ወ.ሓ.ትና ተባባሪዎችዋ ጋር ይዋጋ ነበር። ሃቁ ይሄ ነው። ከትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር፣ በኋላ ህዝባዊ ወያናይ ሓርነት ትግራይ ከተባለው፣ አሁን ኢትዮጵያን እየገዛ፣ እየመዘበረና እያጠፋትም ካለው ግንባር ጋር፣ ኢሕአፓ የነበረው ግንኙነት በአመዛኙ የጠላትነት ግንኙነት ነው። ከህ.ወ.ሓ.ት ምሥረታ ቀደም ብሎ ኢህአሠ ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት ትግራይ ዉስጥ፣ አሲምባ ላይ መሽጎ ነበር። ስለሆነም ሁለቱም ድርጅቶች ትግራይ ዉስጥ ይንቀሳቀሱ ከነበሩበት ወቅት ጀምሮ በመሐከላቸው የነበሩት ግንኙነቶች፣ በውጥረት፣ በጠብ፣ በግጭቶችና በጦርነቶች ይገለጡ የነበሩ ናቸው።

ኢሕአፓ/ሠ በሠላማዊ መንገድ ችግሮቹን ለመፍታት ቢጥርም ጠባብ-ብሔረተኛው ህ.ወ.ሓ.ት. ግን፣ ኢሕአፓ ለማምጣት የሚፈልጋት ትልቅነትዋን የጠበቀች፣ እኩልነትና ፍትኅ (ማኅበራዊ ፍትኅ ጭምር) የሰፈነባት፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስለማይዋጥለት፣ በእነሱ በኩል በሚሰፋፉ ጥላቻ፣ በእነሱ በሚደረግ ትንኮሳ፣ በኋላም በእነሱና ምናልባትም በሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዓቢያ) ትብብር በተከፈተ የኢሕአፓን ሠራዊት፣ ኢሕአሠን፣ ከትግራይ የማስወጣት ጦርነት፣ ከዚያም በኋላ ከወልቃይትና ጠገዴ ጀምሮ እስከ እስከ አርማጭሆ፣ ጭልጋና ጎጃም ከኢሕአፓ/ኢሕአሠጋር ለአያሌ ዓመታት የቀጠሉ፣ ብዙ ሕይወቶችንም የቀጠፉ ጦርነቶች ተካሂደዋል። ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት በመቆሙም ነበር ይህንን ዕምነቱን በነሱ ታጋዮች ዘንድ ለማስጠላት፣ ኢሕአፓን "ዓባይ ኢትዮጵያ" ወይንም "የትልቂቱ ኢትዮጵያ አቀንቃኝ" እያሉ ነበር የሚጠሩት።

የጥላቻቸውም ዋና መሠረት ይሄው ትልቅነትዋ ለተጠበቀ ሆኖም ዴሞክራሲያዊት፣ ዜጎች በኩልነት የሚኖሩባት ኢትዮጵያን ለማምጣት የሚታገል መሆኑ ነው። ይህ እንዴት ይዋጥላቸዋል!? ከሶማሌ ሕዝብ፣ ሶማሊያ ዉስጥ ካሉ የፖለቲካ ሃይሎችና በየጊዜው ከሚመጡ መንግሥቶች ጋር፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም ግንኙነቶች ሊኖረን ይገባል። በኢትዮጵያ ሕዝብና በሶማሌ ህዝብ መሀል ደግሞ በተቻለ መጠን ሁሌም ጥሩ ግንኑነት መኖሩ አስፈላጊ ነው።

ኢሕአፓ የሶማሌ መንግሥትን ማንነት ያውቅ ስለነበረ፣ ከሶማሌ መንግሥት ጋር የነበረው ግንኙነት በዝቅተኛ ደርጃና በጥንቃቄ ይደረግ የነበረ ነው። ደርግን የመሰለ መቅሰፍት እየታገለም ስለነበር መሸሺያም ያስፈልገው ነበርና!! የእንግሊዞች የቅኝ ግዛት የነበረው ሰሜኑ ሶማሊያና በጣሊያኖች ተይዞ የነበረው ደቡቡ ነፃ ወጥተው ከመዋሃዳቸው ከ 1960 (እንደ ግሪጎሪያን ዐመት አቆጣጠር) በፊት በመርዘኞች የእንግሊዝ ቅኝ ገዝዎች ሥር የተቋቋመና የሚበረታታም "ሶማሌ ዮዝ ሊግ" የሚባል ድርጅት አርማውን፣ "ሶማሌ ለዘላለም ትኑር" ከሚል መፈክሩ ጋር ኢትዮጵያ ጅጅጋ ዉስጥ ጭምር እንዲሰቅል አድርገውት ነበር። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ የጣሊያን ፋሽስት ወራሪ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ የነበረው የእንግልዝ ጦር በኢትዮጵያ ቆይታው መርዙን ተክሎ ነው የወጣው።

የተወሰነውን፣ ሶማሊኛ ተናጋሪዎች የነበሩበት የሀገራችን ክፍል፣ "ዘ ሃውድ" በሚል ይታወቅ የነበረውን፣ ሕጋዊ ቁመናው (ስቴቱስ) ያልለየለትና የኢትዮጵያ ወይም የሶማሊያ መሆኑ ወደፊት የሚለይ አስመስሎ አቆይቶት ነበር። ዓላማው ሁለቱ መንግሥቶች ወደፊት የሚጋጩበት መዘዝ መፍጠሩ ነበር። የነፃዪትዋ ሶማሊያ መንግሥት ከተመሠረተ ጀምሮ፣ በነሱ እምነት ሶማሊኛ ተናጋሪዎችን ሁሉ በአንድ ሀገር የመሰብሰብ ግልጽ ፍላጎትና ግብ ነበራቸው። በ 1969 ዓ.ም. (ግሪጎርያን) ሲያድ ባሬ አንድ ሶማልያዊ "ደርግ" መሥርቶ፣ በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ፣ "የምእራብ ሶማሌ ነጻ–አውጭ ግንባር" የሚባል በማቋቋም፣ ሶማልኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበትን የሀገራችንን ክፍል በጦርነት የመገንጠልና፣ የመውሰድ ዓላማውን ማራመድ ጀመረ። ታዲያ በመንግሥት ደረጃ ጦሩን ከማዝመቱ በፊት በቂ ዝግጅት አድርጎ ነበር።

የሶማሌ መንግሥትና በሱም የተቋቋሙትና የሚታዘዙት ወገኖች ምን ዓላማ እንዳላቸው የኢሕአፓ መሥራች አባላትና ሌሎቹም ፍንትው አድርገውም ያውቁ ነበርና ስለሶማሌ መንግሥት ዓላማ ኢሕአፓ ሊሳሳት የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። በሌላ በኩል ኢሕአፓ የብሔር ጭቆና ደርሶብናል በሚሉ ማናቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍሎች ከጭቆና ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል በመርጎ ደረጃ ይደግፍም ስለነበረ፣ የሕዝቡን ብሶት ጆሮ ሰጥቶ ለማዳመጥ ይሞክር ነበር። ኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች ይደርስብናል ብለው የሚያምኑትን ጭቆና ወዲያ ማዶ የሶማሌ መንግሥት ስላለ ችግራቸውን ማዳመጥ፣ ከጭቆና የመላቀቅ መብታቸውን አለማወቅ ስህተት ነውና ኢህአፓ አያደርገውም። በየትም ጭቆና ካለ ያንን ጭቆና ተጠቂው ሕዝብ እንዲታገል ማገዝ እንጂ በሰበብ አስባቡ አይቶ እንዳላየ መሆን ተገቢም ትክክልም አይሆንም። የኢትዮጵያ ጎረቤት የሆነውን የሶማሌ መንግሥት የተስፋፊነት ዕምነትና ሚናን ወገናችን ከሆነው፣ ኢትዮጵያውያን/ት ሶማሌዎች ጭቆናን የመታገል መብት፣ ሁሌም ለይተን ማየት ይገባናል ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። ኢ.ሕ.አፓ በዚያን ጊዜ ሶማሊያ ዉስጥ የነበረው መንግሥት፣ ደርግን የሚመስል፣ ወታደራዊን አምባገነናዊም እንደነበረ ፍንትው አድርጎ ያውቃል። ሆኖም ኢሕአፓ የብሔር ጭቆናን የሚመለከተው አቋሙንና ሌሎችንም የፖለቲካ አቋሞችን እንደ ገበያ ሸቀጥ አይመለከትም።

ኢሕአፓ እንደ ድርጅት ለማንም ሌላ ሃይል፣ ተንበርክኮም፣ ተገዝቶም፣ ሆነ አጎብድዶ በጭራሽ አያውቅም። የሶማሌ መንግሥትን ኢትዮጵያን የመገንጠል ተግባሮች አልደገፈም፣ አልተባበረም። ኢሕአፓ ከሌሎች የፖለቲካ ሃይሎችና መንግሥታት እንደሚገናኘው ከሶማሌዎችም ጋር ይገናኝ ነበር። ሃቁን ማወቅ ለምትፈልጉ፣ በሲያድ ባሬ መንግሥት በኩል ኢሕአፓን ለማግባባትና እዚያው ሶማሌ ውስጥ ደሊጌሽን ጋብዘው "ከምእራብ ሶማሌ ነፃ–አውጭ ግንባር" ጋር ለማገናኘት የተደረገውን ጥረት፣ "የምእራብ ሶማሌ ነፃ አውጭ ግንባር" የተባለው ሃይል፣ በሶማሌ መንግሥት የተመሠረተና ከአሰያየሙ ጀምሮ የሶማሌ

መንግሥትን ተስፋፊነት ያዘለ ስለነበር፣ ኢሕአፓ ጥያቄውን አልተቀበለውም፣ ተገናኝቶ እንኳን ከግንባሩ ጋር አልተነጋገረም። ኢሕአፓ ሶማሊያ ዉስጥም በኅቡእ ነበር የሚንቀሳቀሰው።

በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ዉስጥ፣ ኦጋዴን እየተባለ በሚጠራውና በሌሎችም አካባቢዎች ልክ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ የሶማሌ ብሔረሰብ ተወላጆችን ኢሕአፓ ይመለምልና ያደራጅም ነበር፣ አንዴም በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ጥርጣሬ አልነበረውም። በከፍተኛ የሀገርና የወገን ፍቅር የታገሉትን የኢሕአፓ ጀግኖች ገድል ማኮሰስ፤ አባላቱን መወንጀል፣ ያውም አንዲት ተጨባጭ ማስረጃ ሳያቀርቡ፣ ጥሩ ዕዕምሮ ካለውና በነፃነት ከሚያስብ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አይጠበቅም። "የወፍ ምስክሯ ድምቢጥ!" እንደሚባለው፣ አንዱ ዋሾ ደርግ የሌላውን ደርግ ቃለ ከመመላለስ ውጭ እስቲ አንድ ተጨባጭ መረጃ አምጡ።

"አንዲት ትንኝ እንኳን አልገደልኩም" እንዳለው መንግሥቱ፣ ክህደት የተካናችሁበት ስለሆነ፣ የሃሰት ድርድረቻሁ ይብቃን! እናንተ አብዮታውያኑን በሀገር ዉስጥ ስትጨጭፉ እኮ የሲያድ ባሬው መንግሥት በቂ ጊዜ አግኝቶ፣ ሰፍፊ ዝግጅት አድርጎ ነው ኢትዮጵያን የወረረው። ያኔ የዉስጥን ግድያና ጭፍጨፋውን በማቆም፤ የታሰሩትን በመፍታት፣ ለሁሉም ዜጎች፣ ለኢሕአፓም ጭምር፣ ሀገራዊ ጥሪ ማድረግ ነበረባችሁ! የዚያድ ባሬ መንግስት "የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ግንባር"ን (ኦጋዴን ዉስጥ) አቋቁሞ፣ የኢትዮጵያን ጦር በጉንተላ ከአዳከመ በኋላ ነበር ወረራውን የጀመረው።

የፖለቲካ ሥልጣኑን ያፈቀረው ደርግ በሀገር ዉስጥ በሕዝቡ ላይ ሽብርንና ግድያን ሥራው አድርጎ የነበረበት ወቅት ነው። የሶማሌ መንግሥት ከ 1969 በፊት ጀምሮ፣ መጀመሪያ በመከተል ጣሂር ይመራ የነበረውን ኦጋዴን ዉስጥ የተነሳውን ተቃውሞ፣ በኋላም የነጄነራል ዋቆ ጎቱን ይመራ የነበረውን የባሌ ኦሮሞ እንቅስቃሴ በመደገፍ የሃይለ ሥላሴንና የደርግን መንግሥቶች የማናጋት ሥራዎቹን ሠርተዋል። በርግጥም የኦሮሞ ተወላጆች በፈለጉበት መንገድ እንዳይደራጁ፣ "ራሳቸውን ሶማሌ አቦ" ብለው እንዲሠይሙም የሶማሌ መንግሥት ያደርግ የነበረው ጫና በራሱም በሶማሌ ፖሊሲ ላይ ችግሮችን ፈጥሮበት ነበር። ጄነራል ዋቆ ጉቱና ሌሎች የኦሮሞ ታጋዮች ለእስራትና ለእንግልት ተዳርገውም ነበር። በዚህ የተነሳም ጄኔራል ዋቆ ጎቱ ተላልከው በጄኔራል ጃካማ ኬሎ አማካይነት ከንጉሱ ምኅረት አግኝተው ወደ ሀገራቸው ተመልሰውም ነበር። የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርነት ግንባር በሚል ስያሜ በውጭ ሀገር ተደራጅቶ የነበረው፣ በሼህ ሁሴን ይመራ የነበረው፣ በአመዛኙ ከባሌው እንቅስቃሴ ታጋዮች መሥራችነት የተቋቋመው ከሶማሌ መንግሥት ጋር ከነበሩት አለመግባባቶች የተነሳም ነበር። ነብሳቸውን ይማርና ሼህ ሁሴን ትልቅ ኢትዮጵያዊና ሀገር-ወዳድ ሰው ነበሩ።

የዚያድ ባሬ መንግሥት፣ እንደ ሌሎቹ የዐረብ ሀገር መንግሥታት ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚፈጠሩትን ማንኛቸውም ችግሮች የራሳቸው መጠቀሚያዎች ለማድረግ ነበር የሚጥረው። ዐረቦቹ በአመዛኙ የኢትዮጵያ መንግሥት ከእስራኤል መንግሥት ጋር በነበረው ወዳጅነት የተነሳ፣ ኢትዮጵያን መጉዳት ይፈልጉ ነበር። ሁለተኛም ምን ጊዜም ለኢትዮጵያ የማትተኛዋ የግብፅ ሚና ነበር። የሶማሌ መንግሥት ደግሞ እርዳታ የሚሰጠው ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ፣ እገነጥላለሁ ለሚሉት ነበር።

የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር፣ የሶማሌ-አቦ ግንባር፣ የሲዳማ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር ወዘተ.. በሱማሌ ሪፐብሊክ ውስጥ ሕጋዊ ጽሕፈት ቤቶች ነበሯቸው። በዚህን ወቅት የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት የኤርትራን ጽ/ቤት በደባልነት ይጋራ ነበር። የነዚህ ተገንጣይ ድርጅቶች አባላት በመላው ሶማሊያ የመዘዋወር ነፃነታቸው የተከበረ ከመሆኑም በላይ ከአፍሪካ ውጪ ሊዘዋወሩ የሚያስችላቸው የሶማሊያ ፓስፖርት ነበራቸው። እንዲያውም አንዳንድ የህወሃት መሪዎችና የኤርትራው ግንባር መሪዎች ወደ መጨረሻው አካባቢ የሶማሌ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እስከ ማግኘት ደርሰው ነበር። የሶማሌ

መንግሥት ከነዚህ ግንባሮች ጋር በዕውነትም ኢትዮጵያን የማፍረስ የጋራ ስትራተጂ ነበራቸውና!! አንድ ውስጥ አዋቂ የነበረ ግለሰብ፣ ከጻፈው ዉስጥ "በኢትዮ–ሶማሊያ ጦርነት በተካሄደበት ወቅት ከሱማሌ ጎን ተሰልፈው ኢትዮጵያን የወጉ በካራማራና በኦጋዴን በርሃ የረገፉ የሻአቢያና የወያኔ አባላት ብዙዎች ናቸው ።
ቆስለው በመቃድሾ ሆስፒታል ሲታከሙ የነበሩና የመዳን እድል ያገኙት በተለያዩ የአረብ አገሮች በኩል ወደ ሳሕል በርሀ (የሻዓቢያ ዋና ሠፈር) የገቡ ሲሆን በሞት ከተለዩት መካከል ገሚሶቹ የቀብራቸው ሥነ–ስርአት በመቃድሾ ከተማ ተፈጽሟል። በወያኔና በሻአቢያ ጥምር ሥራ ኢትዮጵያን አፈራርሰው የየራሳቸውን "መንግሥት" ከመሰረቱ በኋላ በሱማሌ ምድር የተቀበሩ የሸአቢያ ተዋጊዎች አጽማቸው ተሰብስቦ ወደ ኤርትራ ተስዷል" ይላል። ትብብራቸውን ቢያውቅም በጦር ሜዳ አብረው መሰለፋቸውን ከታሪክ ዕውነታዊነት አኳያ ኢሕአፓ ራሱ የሚያውቀው ዕውነታ ስላልሆነ ይህንን ጉዳይ እንደገና ማጣራት ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። የኢሕአፓ አባላት የኢትዮጵያ አንድነት እንዳይሸረሸር በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች፣ ብቻ ለብቻ እንኳን ከወራሪው ጦር ጋር በግንባር ተዋድቀዋል። በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር እንደሆነው። የሶማሌን የጥፋት ዘመቻ ለማክሸፍ የዜግነት ግዳጃቸውን ሲወጡ የተሰዉ፣ የተማረኩ፣ በተለያዩ የሱማሌ እስርቤቶች ታስረው የማቀቁ፣ አባላቶቹ ነበሩ።

አሁንም የፋሺስታዊን ደርግ ኢሕአፓን በሕዝብ ለማስጠላት ሲል ያኔ በስለላ መዋቅሩና በካድሬዎቹ በውስጣዊ መመሪያ መልክ ያሠራጨውን የቆረፈደ የማስመሰል–ክስ፣ እስከዛሬ ራሳቸው የፈጸሙት የጭፍጨፋ ወንጀል ባባነናቸው ቁጥር፣ መልሰው መላልሰው ያላዝኑታል። የሲያድ ባሬ "ስትራተጂክ ዝምድና ከኢሕአፓም" ጋር የመፍጠር ሙከራቸው ከከሸፈባቸው በኋላ፣ እንዲያውም የሶማሌ መንግሥትና "የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጭ ግንባር" ኢሕአፓን እንደ ጠላት ቆጥረው በርካታ ጉዳቶች አድርሰውበታል። በርካታ የኢሕአፓ አባላትን አስረዋል፣ አሰቃይተዋል፣ገድለዋል። የኢሕአፓን አባላት ከደርግ ግድያ እያመለጡ በመሸሽ ላይ የነበሩትንም ጭምር፣ ሶማሌዎች እየያዙ እስከ ሶማሊያ ወስደው ያስሩዋቸው ነበርና የታሠሩ አባላቱን ለማስፈታት ጭምር ኢሕአፓ ወደ ሶማሊያ በተደጋጋሚ ሉዕካን ልኳል። የታሰሩበትን አባላት የስም ዝርዝራቸውን ይዘን እንዲፈቱልን የጠየቅናቸውን እንኳን በሙሉ አልፈቱልንም። መቅደሾ፣ ቆርዮሌና ሸለምቦጥ፣ በሌሎችም ማጎሪያዎች በርካታ ጓዶችን አስረው ጉዳት አድርሰውባቸዋል፣ ደብዛቸውንም ያጠፏቸው አሉ። ኢሕአፓን ጠንቅቀው የሚያውቁ ወገኖች አብዛኛዎቹ የኢሕአፓ አባላት ለአንድ ሀገር ኅላዌና ለሕዝብዋ በእኩልነት አብረው መኖር ካላቸው ጽኑ ዕምነት በመነሳት ነበር የታገሉት።

የኢሕአፓ አባላት ለመብት፣ ለነፃነት፣ ለሕዝቡ እኩልነት፣ ለማኅበራዊ ፍትኅ፣ ሲታገሉ ከባድ መስዋዕት ከፍለዋል። ኢሕአፓ ጭቆናን አጥብቀው ከሚቃወሙ፤ በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ፤ ለዴሞክራሲና ለፍትህ ከሚታገሉ ወገኖችን በመደገፍ የትግላቸው አጋር ሊሆን ይችላል እንጅ የባንዳ ሥራ ሠርቶም አያውቅ ወደፊትም አይሠራም ። ኢሕአፓ ትናንትም ዛሬም ወደፊትም አገርን በሚንድ ሕዝብን በሚያዋርድ ነውረኛ ተግባር ዉስጥ አልተሳተፈም፣ አይሳተፍምም ። የኢትዮ–ሶማሊያ ጦርነት ወቅት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች እንኳን ከሱማሌ ጦር ጋር አብረው ሊቆሙ ይቅርና በሶማሊያም ዉስጥ ጭምር እየተሳደዱ ነበር። የስደተኛነት መብት እንኳን ተነፍገው ነበር።

ህይወታቸውን ከሰው–በላው ደርግ ለማትረፈ ሸሽተው፣ ከእሥር አምልጠው፣ ወደሶማሊያ ገበተው የነበሩት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በሶማሊያ እስርቤቶች ውስጥ መከራን ሲገፉ እንደነበር ሁሉም ዕውነተኛ ዜጋ የሚያወቀው ጉዳይ ሆኖ ሳለ

ኢሕአፓ ከሶማሊያ መንግሥት ጎን ተሰልፎ ውድ አገሩን ወግቷል የሚለው በሬ–ወለድ ዓይነት ውሸትና የሃሰት ውንጀላ ከዚያ ከሶማሊአ የእሥር ሲያል የተረፉ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዮች በሕይወት እያሉ መስማታቸው ለጆሮ የሚቀፍ ለኅሊና የሚዘገንን ነገር ነው። ኢሕአፓ. ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ኤል.ኤፍ) ጋር፣ በድርጅት ደረጃ የቅርብ ግንኙነትም ሆነ ትብብር የረጅም ጊዜ ትብብር ኖሮት አያውቅም። አልፎ አልፎ የተደረጉ ውይይቶችና በግንባር ደረጃ ለመተባበር ወደ መድረኮች የኦ.ነ.ግ. አመራር አባላት ብቅ ብለው እንደገና ስለሚሸሹ፣ (ለምሣሌ ኢ.ተ.ፖ.ድ.ኅ. የሚባል ኅብረት ፓሪስ ዉስጥ ሲመሠረት፣) አብዛኛውን ጊዜም የያዙትን የመገንጠል አጀንዳ ስለሚያራምዱ፣ በኋላም በብዙ ዕምነቶቹ እነሱኑ ከሚመስለው ከህ.ወ.ሓ.ት. ጋር ተሳስረው አሁን ሀገራችን ዉስጥ የተፈጠረውን የብጥብጥ ሁኔታ እያመጣ ያለውን የመገንጠልና የማስገንጠል ቋሚ ስጋት በሀገራችን አመጡ። ኦነግ ራሱን ለውጦ ኢትዮጵያዊነቱን መቀበል ስላዳገተው፣ ዘላቂና አስተማማኝ ግንኙነቶች ከኢህአፓ ጋር እንኳን ለመፍጠር አልቻለም ።

የመገንጠል አጀዳን በግልፅ የመይቃወሙ ቡድኖችንና ድርጅቶችን እያነፈነፈ ሲፈልግ ነው የኖረው። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነትን፣ አንዴ አጥብቆ የሚይዘው፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅማ–ጥቅም ወይንም ሀገራዊ አንድነትን የሚጠሉትን ለማባበል በማሰብ፣ ይህን "አታንሱብኝ" እያለ የሚዘባበትበት አይደለም። ኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነቷን ጠብቀን፣ ዴሞክራሲያዊት አድርገን፣ የህግ የበላይነትን አስፍነን፣ በተጨማሪም ማኅበራዊ ፍትኅ የሰፈነባት ሀገር እናድርጋት፣ ሕዝቡን ባለሙብት እናድርግ ነው የሚለው። ይህ ታዲያ ለጠባብ ብሔረተኞችና ለአድር ባዮች አይመችም።

ኢሕአፓ. ከሱዳን መንግሥት ጋር የነበረው ግንኙነት በርካታ ውጣውረዶች የነበሩት ነው። መጀመሪያ የኤል ኑሜሪ መንግሥት በነበረበት ጊዜ ሱዳን ዉስጥ በይፋ የሚደገፉት የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትንና እንዲሁም በእንግሊዝኛ መጠሪያው ኢ.ፒ.ዲ.ኤ. ይባል የነበረው፣ በአሜሪካን ይደገፍ የነበረውን፣ ድርጅት ነበር። ይኸም በኢትዮጵያ ዉስጥ ደርግን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የግራ ዝንባሌ ያላቸውን የፖለቲካ ሃይሎች ከምዕራባውያኑ፣ ከዐረብ አድሃሪዎች፣ ከኢራኑ ሸህ ፓህሌቪ ጭምር ፀረ ግራ ትልቅ ሤራ ስለነበረ። ሆኖም ምናልባት በኢሕአፓና በደርግ መሐከል በነበረው ልዩነትና ግጭቶችም የኢትዮጵያን መንግሥት ከማናጋት እሳቤ፣ ኢሕአፓንም አይቶ እንዳላየ የመመልከት አዝማሚያ ስለነበራቸው ኢሕአፓም በሁኔታው ድምጡን አጥፍቶ ይጠቀምበት ነበር። ለበርካታ ዓመታት ቢሮ አልከፈተም ሆኖም ያደራጅና ይንቀሳቀስም ነበር።

በኋላ አጋር ያደርጓቸው ድርጅቶች እየተዳከሙ መጥተው ኢሕአፓ ግን እንደተመኙት ሊጠፉላቸው ስላልቻለ አሁንም ደርግ እንዲወድቅ ይፈልጉ ስለነበረ ኢሕአፓም የበለጠ ዕውቅና ሊያገኝ ችሎ ነበር። በኋላ ሱዳንም ከኢሕአፓ ዕምነት አኳያ ደጋግሞ፣ ከአንዴም ሁለቴ፣ "ወጥ–ረገጠ"! አንድ ጊዜ በደርግ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ ዕቅድ አውጥተው፣ ለሁሉም ኢትዮጵያ ዉስጥ ያኔ ይንቀሳቀሱ ለነበሩ፣ "ነፃ–አውጭ" ይባሉ የነበሩ ድርጅቶች የተወሰኑ ወታደራዊ ዒላማዎችን እንዲያጠቁ የተቀነባበረ ስትራተጂ አወጡና አከፋፈሏቸው። ምናልባት በእነዚሁ ግንባሮች ምክር ሊሆን ይችላል፣ በሀገር ዉስጥ ኢሕአፓ የኀብዕ ድርጅታዊ መዋቅር ጥንካሬ ስለነበረውም፣ የኢሕአፓን የአመራር አባል አስጠርተው፣ ያኔ የሱዳን ምክትል ፕሬዜዳንት በሆነ ግለሰብ አማካይነት፣ "የዐባይን ድልድይ እንዲደረምስ" ጠየቁት።

ይህ ታዲያ ከፍተኛ የሀገርና የወገን ፍቅር ላለው ኢሕአፓ የሚዋጥለት አልነበረምና፣ እዚያው ፊትለፊት ወዲያውኑ "ይህንንማ በፍፁም አናደርግም" ነበር ያልናቸው። ድልድዩ እኮ የሕዝቡ መገልገያ ነው። የሰሜኑና የደቡቡ ሕዝብ ሁለንተናዊ ትስስርና ግንኙነት ይጎዳልና ኢሕአፓ ሕዝቡን የሚጎዳ ጥፋትማ አያደርስም አልናቸው። ጠባችን ከደርግ ጋር እንጂ ከሸዝባችን ጋር ስላልሆነም! አስፈራሩን። በእምቢታችን ፀንተን፣ እነሱም እንደተመኙት፣ "መሣሪያቸው" ሳያደርጉን ቀጠልን። ጊዜ እየጠበቁልን

አድብተው ቆዩ። ለሁለተኛ ጊዜ ደርግ በጣም እየተዳከመ መጥቶ በሰሜናዊው የሀገራችን ክፍሎች በርካታ አካባቢዎችን መቆጣጠር ተስኖት ነበር። ኢሕአፓ ታዲያ ከገጠሙት አያሌ ችግሮቹ ወጥቶና አገግሞ እንደገና በመጠናከር በደቡብ ጎንደርና በበርካታ የጎጃም አውራጃዎች ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን አጠናክሮ ነበር።
ማዕከሉን ቋራን ሳይለቅ በርካታ አካባቢዎችን ነፃ አውጥቶ ሕዝቡም ራሱን ማስተዳደር ጀምሮ ነበር። ያኔ ኢሕአፓ ሱዳንም ዉስጥ በመጠኑም ቢሆን ላላ ብለውለት ቢሮዎችን ከፍቶ መነቀሳቀስ ችሎ ነበር። አሁንም ሱዳን የደርግን መዳከም በመረዳት ሌላ ሙከራ ላይ ተሰማራ። ከመተማ እስከ አይማ ወንዝ ያሉትን፣ ወህ ገብና ለም፣ ደን ለበስ የኢትዮጵያ መሬት፣ አሁን ከህ.ወ.ሓ.ት. የተቸሩትን የድንበር አካባቢዎችን፣ በሀብታም ገበሬዎች እንዲታረሱ ለማድረግ ጥበቃ የሚያደርጉ ወታደሮችን መርትይራድ፣ በሚባል የወሰን አካባቢ ላይ በማስፈር ለመስፋፋትና ስፍራውን ለመያዝ መንቀሳቀስ ጀመረ። የአካባቢው ሕዝብና ኢሕአፓም ይህ ወረራ በዝምታ የሚታለፍ ሊሆን እንደማይገባው ተማምነው የታጠቁ አርበኞች ሱዳናውያኑን ለማስለቀቅ እርምጃዎችን መውሰድ ጀመሩ።

ያኔ ታዲያ የሱዳን ባለሥልጣኖች ኢሕአፓን እንደገና ማስፈራራት ጀመሩ። “ቢሮ አችሁን እንዘጋለን!” ይሉ ገቡ። የኛ መልስ ሕዝቡ እኮ መሬቱ የኛ ነው እያለ ነው፤ አልናቸው። እነሱም “ያለ እናንተ ይሁንታ ይህ አይሆንም” ማለታቸውን ቀጠሉ። ደፈር ብለውም እነዚያን የታጠቁ አርበኞች ለመጉዳት በወታደራዊ ሃይል ወደ ነፃ አካባቢያችን ጎራ አሉ። ከኢሕአፓ ሠራዊት አይቀጡ ቅጣት፣ ገጠማቸው። ጉዳት ደረሰባቸው፣ አፈገፈጉም። ያኔ የነበራቸው አማራጭ፣ አድብተው ጊዜ መጠበቅ ነበርና ለጊዜው ሽንፈት ተቀብለው ተባረሩ። ህ.ወ.ሕ.ትንና ሽ ዓቢያን አሰባስበው በ 1991 ላይ በኢሕአፓ ላይ እስከዘመቱ ድረስ ያንን አካባቢ አልደፈሩትም ነበር። በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ በሃይልና በጉልበት ራሱን ጭኖ የነበረውን፣ የተቃወመውን ቀርቶ ልዩነት ያሳየን ሁሉ ያስር፣ ያሰቃይ፣ ያርድና ይጨፈጭፍ የነበረውን፣ የመደራጀትና የመነቀሳቀስ መብት ነፍጎ ተቃዋሚዎችን ሁሉ ወደ አመፅ የገፈተረውን ወታደራዊ ደርግ፣ በሕዝብ ያልተመረጠ በመሆኑ ለኢሕአፓ “... ሕገወጥ፣ አምባገነናዊ፣ በተግባሮቹም ፋሽስታዊም” ነበር።

ስለሆነም መቼም ኢሕአፓ ማንኛውንም ድርጅት ወይንም መንግሥት ሲገናኝ፣ ደርግን ማስፈቀድ እንዳልነበረበት አዕምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ አይስተውም። ዛሬ ሀገራችን ውስጥ ያለውን አስከፊና አስጊም ሁኔታዎች በትግሉ ለመለወጥ የተነሳን ወጣት ትውልድ ማሳወቅ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። የቀዳሚ ትውልዶች አባላት የሚያውቁትን ሁሉ ዕውነቱን፣ ሳያውገረግሩ፣ ሳይዋሹ፣ እንዲነግሯቸው፣ እንዲያስተምሯቸው፣ ጽፈው እንዲተዉላቸውም ይጠበቃል። በሙሉ የማይታወቅ፣ የሚጠራጠሩት ነገር ሲኖርም ጉዳዩን በጥርጣሬ መልክ ማስቀመጥ ይጠበቃል።ያለምንም ማስረጃ ግን ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶችን፣ ስለማንወዳቸው ብቻ፣ ወይንም ከሌላ ተልዕኮ ተነስተን፣ በሃሰት መክሰስ ወጣቱን ትውልድ መበከል እንጅ ማስተማር አይሆንም። የመደብ ልዩነትና ተዛማጁ የርዕዮተ ዐለም ልዩነት ኢትዮጵያ ዉስጥ በፊትም ነበር፣ አሁንም አለ፣ ወደፊትም ይኖራል። በተለያዩ መንገዶች ሃብት ያፈሩ፣ የከበሩ፣ የናጠጡም ከበርቴዎች በየሀገሮቹ አሉ።

በሌብነት፣ የሕዝብ ሃብት ስልጣናቸውን ተገን አድርገው የሚዘርፉ አሉ። “ሀብታም ከሆኑት” መሐል ስግብግቦችና በሃብት ላይ ሃብት ማፍራት ብቻ ዓላማቸውም፣ ህልማቸውም የሆነ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ ፋብሪካዎች ስለሚያደርሱት ብክለትም ሆነ መሰል አካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች፣ ስለ ሠራተኞች የኑሮና የጤና ሁኔታ፣ ወ.ዘ.ተረፍ ቁብ የማይሰጡ አሉ። ቀረጥ ላለመክፈል ሃብታቸውን ከቀረት–ነፃ በሆኑ ደሴቶች የሚሸጉቱ ሞልተዋል። በየሃሰ ሳንደረድር የሃሳብ ፍጭት ማድረግ ነው

የሚጠበቅብን። ደርግ በተባለው መቅሰፍት ቡድን ዉስጥ በአውራ ተዋናይነት ተሠልፋችሁ የነበራችሁ፣ በቅድሚያ ጥፋታችሁን እመኑ። ላደረሳችሁት ጭፍጨፋ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ። “ቀደም ብሎ አንድ ሌላ ታጋይ ትውልድ” ከመተሩ፣ ከህ.ወ.ሓ.ት. ነፍስ–ገዳዮች ከማይሻሉ፣ የሌላ ጊዜ ወንጀለኞች፣ ለአዲሱ ትውልድ ምክር ለመለገስ ከመሞከራችሁ በፊት፣ ያውም በቅጥፈቶች አጨማልቃችሁ ለመበከል ከመንደርደራችሁ በፊት፣ የራሳችሁን ጥፋቶች አምናችሁ፣ ክፉኛ ከበደላችሁት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ያስፈልጋችኋል።

የደርግና የባዕድ ተላላኪዎች ውሸት ይጋለጣል!!

የኢሕአፓ ጀግኖች ትክክለኛ ታሪካዊ ይወደሳል!!

ቄሮ፤ ፋኖ፤ዘረማና ነብሮ በኢትዮጵያዊነት ያሸበርቃሉ!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!